# የምግብ ድጎማዎች (SNAP)

## መብትዎን ይወቁ!

Legal Aid Society
OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

### የምግብ ድጎማዎች ምንድን ናቸው? (SNAP)



የምግብ ድጎማዎች (ወይም ስናፕ (SNAP)) ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች ምግብ መግዛት እንዲችሉ ያግዛሉ። የምግብ ድጎማዎች EBT በሚባል ካርድ በኩል ይሰጣሉ።

በምግብ ድጎማዎች አብዛኛዎቹን ምግቦች መግዛት ይችላሉ። የተዘጋጁ ምግቦችን፣ ሳሙና፣ አልኮል፣ ሲጋራ፣ ወይም ምግብ ያልሆነ ማንኛውም ነገር መግዛት አይችሉም።

### የምግብ ድጎማዎች ማግኘት እችላለሁኝ?

የምግብ ድጎማዎች "ለቤተሰብ" ይሰጣሉ። ቤተሰብ ማለት በበጋራ የሚኖር እና ምግብ የሚገዛ እና የሚያበስሉ ማንኛውም ሰዎች ናቸው።

ሰንጠረዡ የሚያሳየው የምግብ ድጎማ ማግኘት እንደሚችሉ እና መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ ነው።

| የቤተሰብ ብዛት | የምግብ ድጎማ ሊያገኙ የሚችሉት የቤተሰብዎ ወርሃዊ የገቢ መጠን ከዚህ ካነሰ ነው… | *የመጨረሻው* ወርሃዊ የጥቅማጥቅም መጠን |
|---|---|---|
| 1 | $1,383* | $234 |
| 2 | $1,868* | $430 |
| 3 | $2,353* | $616 |
| 4 | $2,839* | $782 |
| 5 | $3,324* | $929 |
| 6 | $3,809* | $1,114 |
| 7 | $4,295* | $1,232 |
| 8 | $4,780* | $1,408 |

*ከላይ ከተጠቀሱት መጠኖች ውጪ ተጨማሪ ገቢ ያለዎት ከሆነ፣ ቤተሰብዎ ውስጥ በዕድሜ የገፉ ሰው ወይም አካለስንኩላን ያሉ ከሆነ የምግብ ድጎማ ማግኘት ይችላሉ። ጥያቄዎች? ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ።

የምግብ ድጎማ ማግኘት እንደሚችሉ ለማወቅ፣ ወደዚህ ይሂዱ https://www.dchunger.org/calculator/.

### የአሜሪካ ዜግነት የለኝም። የምግብ ድጎማዎች ማግኘት እችላለሁኝ?

**ሊሆን ይችላል።** የአሜሪካ ዜግነት የሌላቸው አንዳንድ ሰዎች የምግብ ድጎማ ሊያገኙ ይችላሉ። ወደ ሌጋል ኤድ በራሪ ወረቀት፣ **"የአሜሪካ ዜግነት ከሌለዎት የሕዝብ ጥቅማጥቅም ማግኘት።"** ላይ ይሂዱ።

ምንም እንኳን የምግብ ድጎማ ማግኘት ባይችሉም፣ ለልጅዎ እና ለሌሎች የቤተሰብ ዓባላት የ ኢሚግሬሽን ምድብ ሁኔታቸው የምግብ ድጎማ ማግኘት የሚያስችላቸው ከሆነ አሁንም ማመልከት ይችላሉ።

ለሚያመለክቱላቸው ሰዎች የኢሜግሬሽን አቋማቸውን ብቻ መፃፍ ያስፈልጎታል። ተጨማሪ መረጃ መንግስት መጠየቅ አይችልም።

### እንግሊዘኛ በደንብ የማልናገር ከሆነ ማመልከት እችላለሁኝ?

**አዎ።** ሕግ የሚለው መንግስት በእርስዎ ቋንቋ ሊያግዞት ይገባል ነው። የሚፈልጉትን ኤጀንሲ በእርስዎ ቋንቋ እገዛ እንደሚሹ ይንገሯቸው።

***የምግብ ድጎማ ላይ እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ ለማወቅ ቀጣዩ ገጽ ላይ ይሂዱ።***

## የምግብ ድጎማ ላይ እንዴት ማመልከት እችላለሁኝ?

**አንድ ማመልከቻ ላይ** የምግብ ድጎማ፣ ታንፍ(TANF)፣ ሜዲኬድ እና ዲሲ የሕክምና አልያንስን ጨምሮ**ሁሉም** የሕዝብ ጥቅማጥቅሞች ላይ ማመልከት ይችላሉ።

**ቅደም ተከተል 1፦ የሚያስፈልጎትን ሰነዶች ያዘጋጁ።** *ኦርጅናሎቹን እንዳይልኩ! በፎቶ ያንሱት ወይም ኮፒ ያድርጓቸው።*

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የእርስዎ የፎቶ መታወቂያ። | የእርስዎ የማህበራዊ ደህንነት ካርድ (ያለዎት ከሆነ) | የገቢ ምንጭ ማሳያ ( ልክ እንደ የክፍያ ማረጋገጫ) | የመኖሪያ አድራሻ (ልክ እንደ ክፍያ ደረሰኝ) | በቤተሰብዎ ውስጥ ለሚኖሩ እያንዳንዱ ሰዎች የልደት ምስክር ወረቀቶች |

**ቅደም ተከተል 2፦ ከአራት መንገዶች ውስጥ በአንዱ ያመልክቱ፦**

**በአካል በመገኘት፦** ከእነዚህ **ESA አገልግሎት ማዕከሎች** አንዱ ላይ ይሂዱ። በሚያመለክቱበት ሰዓት ማረጋገጫ ደረሰኝ ይጠይቁ።

- **አኖክስቲያ የአገልግሎት ማዕከል (Anacostia Service Center)**
  2100 Martin Luther King Jr. Avenue SE
  (202) 645-4614
- **ኮንግረስ ሃይትስ አገልግሎት ማዕከል (Congress Heights Service Center)**
  4001 South Capitol Street SW
  (202) 645-4546
- **ኤች ስትሪት አገልግሎት ማዕከል (H Street Service Center)**
  645 H Street NE
  (202) 698-4350
- ***[ተዘግቷል]* ፎርት ዴቪስ አገልግሎት ማዕከል (Fort Davis Service Center)**
  3851 Alabama Avenue SE
  (202) 645-4500
- ***[ተዘግቷል]* ታይለር ስትሪት አገልግሎት ማዕከል (Taylor Street Service Center)**
  1207 Taylor Street NW
  (202) 576-8000

**በስማርት ስልክዎ፦** ኦንላይን የመተግበሪያ መደብር ላይ የ **District First** መተግበሪያን ያውርዱ። በስልክዎ ላይ ያመልክቱ። የተሰጥዎትን ማረጋገጫ ቁጥር ጽፈው ያስቀምጡ።

**ኦንላይን፦** ኦንላይን በዚህ ላይ ያመልክቱ https://dcbenefits.dhs.dc.gov። የተሰጥዎትን ማረጋገጫ ቁጥር ጽፈው ያስቀምጡ። ያስረከቧቸውን ነገሮች ቅጂ ያስቀምጡ።

**ደብዳቤ፦** ማመልከቻውን እዚህ ላይ ያግኙ https://dhs.dc.gov/node/117542። አገልግሎት ማዕከል ላይ ማመልከቻውን እና የሰነዱን ቅጂዎችን ይላኩ(ወደ ግራ ተዘርዝሯል)። በማመልከቻዎ ላይ በደብዳቤ እንዳላኩ ያሳውቁ። ***ይሄ አማራጭ አይመከርም።***

## ከማለከትኩኝ በኋላ፣ ማመልከቻዬ ላይ ውሳኔ በምን ያህል ፍጥነት ማግኘት እችላለሁኝ?

በአብዛኛው፣ መንግስት ማመልከቻዎን ለማስተናገድ **30 ቀናቶች** አሉት። ማመልከቻዎ በ **7 ቀናት** (“የተፋጠነ መስተንግዶ”) ውስጥ እንዲስተናገድ በማመልከቻ መጠየቅ ይችላሉ የሚከተሉት ከተሟሉ፦

- $150/በወር የሚያገኙ ከሆነ **እና** ቁጠባዎ ላይ ከ $100 በታች ያለዎት ከሆነ፣ ***ወይም***
- የቤት ክራይዎ ወይም የፍጆታ ወጪዎችዎ ከገቢዎ በላይ ከሆኑ።

ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካገኘ ወይም ካላገኘ በደብዳቤ ወይም በመተግበሪያው ላይ ማስታወቂያ ይደርሶታል።

## የምግብ ድጎማ አላገኘሁም ወይም ማግኘት አቋርጫለሁኝ። ምን ማድረግ እችላለሁኝ?

ይግባኝ የመጠየቅ መብት አሎት። የእርስዎ የምግብ ድጎማዎች እንደተከለከሉ፣ እንደተቋረጡ፣ ወይም እንደተቀነሱ የሚያሳይ ማስታወቂያ በደረሰዎ **90 ቀናት ውስጥ** ይግባኝ መጠየቅ አለብዎ። ይግባኝ ለመጠየቅ ሶስት ቅደም ተከተሎች አሉ።

**ቅደም ተከተል 1፦** የይግባኝ ቅጹን ያግኙ። ወደዚህ ይሂዱ https://oah.dc.gov/node/154252 ወይም OAH ን በ (202) 442-9094 ላይ ይደውሉ።

**ቅደም ተከተል 2፦** የይግባኝ ቅጹን ይሙሉ።

**ቅደም ተከተል 3፦** ከእነዚህ መንገዶች ውስጥ <u>በአንዱ</u> ቅጹን ይሙሉ፦

| | | |
|---|---|---|
| በዚህ **ኢሜይል** ይላኩት oah.filing@dc.gov. | የአስተዳደር ሰሚዎች ቢሮ (Office of Administrative Hearings)፣ 441 Fourth Street NW, Suite 450N, Washington, DC 20001 **በአካል በመግኘት ያምጡት**። *የቅጹን ቅጂ ያስቀምጡ።* | በግራ በኩል የሚገኘው አድራሻ ላይ **በደብዳቤ** ይላኩት። *የቅጹን ቅጂ ያስቀምጡ። የላኩበትን ቀን ጽፈው ያስቀምጡ።* ***ይሄ አማራጭ አይመከርም።*** |

*የክስ የሚሰማበትን ቀን በመጠባበቅ የምግብ ድጎማውን ይዘው ማቆየት ይችላሉ። ጥቅማጥቅሞችዎ ከመቆረጣቸው ወይም ከመቀነሳቸው በፊት ክሱ እንዲታይልዎ ይጠይቁ (በዚህ ማስታወቂያው ላይ ይሄንን ቀን ያግኙ) ድንገተኛ እንደሆነ ይናገሩ።*

**እገዛ ይፈልጋሉ?** (202) 628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ https://www.legalaiddc.org/online-intake/።